ጥቁር አንበሳ
TIKUR ANBESSA

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

“ሆስፒታሉን የኒኩሊየር ሕክምና ማሰልጠኛ ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው”

ፕሮፌሰር አንዱዓለም ደነቀ
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

ሶሎሞን በየነ

በኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት ቅብብሎሽ ሥርዓት ውስጥ የመጨረሻውና ከፍተኛው የጤና ክብካቤ መስጫ የሆነው የአዲስ አበባ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፤ በአገሪቱ ከሚገኙት ሆስፒታሎች ትልቁና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ነው። ከአራቱም የአገሪቱ ማዕዘን ለተሻለና ለከፍተኛ ሕክምና የሚመጡ ታካሚዎች መዳረሻ የሆነው «አንድ ለእናቱ» ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል፤ በትንሹ በዓመት ለ500 ሺህ ተመላላሽ እና ለ20 ሺህ ተኝተው ለሚታከሙ ሕሙማንን አገልግሎት ይሰጣል።

ዘመናዊ የምዕራባውያኑ ሕክምናን በአገሪቱ ያስተዋወቁ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ሐኪሞችን ያፈራው ይህ ሆስፒታል፤ የሕክምና ትምህርት ለሚማሩ ቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎች በተግባር የተደገፈ እውቀትና ክሕሎት በማስጨበጥ አያሌ የሕክምና ባለሙያዎችን በማፍራት አገሪቱ ዛሬ ላይ በዘርፉ ለደረሰችበት ደረጃ የጎላ ድርሻ አበርክቷል፤ እያበረከተም ይገኛል። ከዚህ በመነሳት የተቋሙ ታሪካዊ አመሰራረት፣ ባለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት የተጓዘባቸው እርቀትና በጉዞው የገጠሙት ተግዳሮቶች እንዲሁም በቀጣይ የት ለመድረስ አቅዶ እየሠራ እንደሚገኝ በሚመለከት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፕሮፌሰር አንዱዓለም ደነቀን አነጋግረን ተከታዩን አጠናቅረናል።



ፎቶ አዮብ ተፈሪ

አዲስ ዘመን:-የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ታሪካዊ ዳራ ምን ይመስላል?

ፕሮፌሰር አንዱዓለም:- ሆስፒታሉ ተመርቆ ወደ ሥራ የገባው ጥቅምት 24 ቀን 1966 ዓ.ም ነው። የመሰረት ድንጋዩ ተጥሎ ግንባታው የተጀመረው ደግሞ ጥቅምት 24 ቀን 1954 ዓ.ም ነው። ግንባታውም 12 ዓመት ፈጅቷል። ይህ ማለት ተመርቆ ወደ ሥራ ከገባ ድፍን ግማሽ ምዕተ (50) ዓመት ሆኖታል። ግንባታው ከተጀመረበት ደግሞ 62 ዓመት ሞልቶታል።

በሕዝብ የተባበረ ክንድ የተገነባው ይህ ሆስፒታል የአፄ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ልጅ በሆነው በልዑል መኮንን የሐረር መስፍን መታሰቢያ የተሰየመ ነበር። ሆስፒታሉ ዛሬ ላይ የሚጠራበትን “ጥቁር አንበሳ” የሚለውን ስያሜ ያገኘው ከ1966ቱ አብዮት በኋላ ነው። “ጥቁር አንበሳ” ማለት የፋሺስት ጣሊያን ወረራ ለመመከት በሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ስልጠና የወሰዱ ወጣቶች ስያሜ ነው።: ለእነዚህ ፋሺስት ጣሊያንን በሽምቅ ውጊያ ተፋልመው ድል ላደረጉ ጀግኖች አርበኞች መታሰቢያ ይሆን ዘንድም በ1967 ዓ.ም ሆስፒታሉ ጥቁር አንበሳ ሊባል ችሏል። በመሆኑም ጥቁር አንበሳ የሚለው ስያሜ “ሞአ አንበሳ ዘእመ ነገደ ይሁዳ ከሚለው” ከሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ሥያሜ ጋር የተያያዘ አይደለም።

ሆስፒታሉ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ በሕክምናው ዘርፍ የራሱን የታሪክ አሻራ ያሳረፈ ሲሆን፤ ሆስፒታሉ ተመርቆ ወደ ሥራ እንደገባ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተከፍቶ የነበረው የሕክምና ትምህርት ቤት ወደ ሆስፒታሉ እንዲመጣ ተደርጓል። በዚህም ሆስፒታሉ የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት ከመሆኑ ባለፈ የመማር ማስተማርና የምርምር ሥራ የሚካሄድበት ተቋም ነው።

በኋላም መንግሥት በሕክምናው ዘርፍ በተበጣጠሰ መንገድ አገልግሎትና ትምህርት ይሰጡ የነበሩ ተቋማትን አንድ ላይ በማደራጀት ያለውን ውስን ሃብት በጋራ ተጠቅሞ የተሻለ ውጤት ለማምጣት በማለም፤ አራት የሕክምና ትምህርት ቤቶችን (የሕክምና ትምህርት ቤት፣ የሕብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት፣ የነርሲንግና ሚድዋይፊሪ ትምህርት ቤት፣ የፋርማሲ ትምህርት ቤት) ወደ አንድ በማምጣት በ2002 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅን አቋቁሟል። ይህንን ተከትሎ ቀደም ሲል “አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ትምህርት ቤት” ይባል የነበረው፤ “አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል” የሚለውን ስያሜ ሊይዝ ችሏል። ስለዚህ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በዚሁ ኮሌጅ ሥር የሚገኝ አንድ ትልቅ ተቋም ነው።

አዲስ ዘመን:- ሆስፒታሉ ባለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት የተንዘባረቸው እርቀቶችና ያስመዘገባቸው ውጤቶች ምን ምን ናቸው?

ፕሮፌሰር አንዱዓለም:- በጤና አገልግሎቱ ዘርፍ መደበኛ ወይም አነስተኛ ሕክምና ከምንላቸው ጀምሮ፣ እስከ ከፍተኛ የጤና አገልግሎቶች ለመስጠት የሚያስችለው ቁመና ላይ ደርሷል። ሆስፒታሉ የመጨረሻውና ለከፍተኛ ሕክምና የሚላኩ ታካሚዎች መዳረሻ ሲሆን፤ ለአብነት እንደ ልብ ቀዶ ሕክምናና ከፍተኛ የካንሰር ሕመምን በጨረር ማከም ከጥቁር አንበሳ ውጭ በሌሎች የመንግሥት ሆስፒታሎች ቀደም ሲል አይሰጠም ነበር።

በትምህርቱ ዘርፍ ደግሞ በቅድመ ምረቃ ያውም በአንድ ትምህርት ዘርፍ ነበር ማስተማር የጀመረው። ዛሬ ላይ ግን በቅድመ ምረቃ በስምንት የትምህርት ፕሮግራሞች እያስተማረ ይገኛል። በድህረ ምረቃ ደግሞ ከምንም ተነስቶ (የማስተርስ፣ የፒኤችዲ፣ የስፔሻሊቲና የሰብ ስፔሻሊቲ) በጥቅሉ ከ100 በላይ የትምህርት አይነቶች ኮሌጁ ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ ይገኛል።ይህም የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ከፍ እያለ ደረጃውን እያሳደገ መምጣቱን የሚያሳይ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በምርምር ዘርፍ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጁ ቀዳሚ ነው። ኮሌጁ የሚያከናውናቸው ምርምሮች የአገሪቱን የጤና አገልግሎትና የትምህርት ዘርፍ ከማሻሻል አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይሁን በአፍሪካ ያለውን ደረጃ ወይም ቦታ በከፍተኛ ደረጃ አሻሽሎታል። እንዲሁም ያካሄዳቸው ጥናትና ምርምሮች ዓለም አቀፍ ትብብሮችን በከፍተኛ ደረጃ አምጥተዋል።

አዲስ ዘመን:- ሆስፒታሉ ባለፉት 50 ዓመታት ጉዞው ያሳካቸው ስኬቶች እንዳሉ ሁሉ ያጋጠሙት ፈተናዎች ምን ምን ናቸው? ፈተናዎቹን ያስፈበት ጥበብ ምን ይመስላል?

ፕሮፌሰር አንዱዓለም:- አንድ ሥራ ሲሠራ ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ አይሆንም። ብዙ ተግዳሮቶች ይኖሩታል። ሀገራችን ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ የምትመደብ እንደመሆኗ መጠን፤ ተግዳሮቶች እንዳሉ እሙን ነው። ከገጠሙን አንኳር ችግሮች የመጀመሪያው የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ነው። ምንም እንኳን በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ብንገነባም፣ በተለይ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነና ማሰልጠን የሚችል የሰው ኃይል እጥረት አሁንም አለብን።

ይህንን ችግር ለማቃለል የባለሙያ ልውውጥ ፕሮግራም በስፋት እንጠቀማለን። በዚህ ፕሮግራም መሰረት አንደኛ በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ወደ ተቋሙ መጥተው በተቋሙ እንዲሠሩና አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል። ሁለተኛ ደግሞ የውጭ ባለሙያዎች አገልግሎቱን ሲሰጡ የተቋሙ ባለሙያዎችን በዛው እያሰለጠኑና እያስተማሩ እንዲሄዱ እናደርጋለን። በብዙ መስኮች ይሄ ይደረጋል። ሌላው ዓለም አቀፍ ትብብሮችን ተጠቅመን ወደ ተለያዩ የዓለም አገሮች ባለሙያዎቻችንን እየላክን ለአጭርና ለረጅም ጊዜ ሰልጥነው እንዲመጡ እናደርጋለን። በነዚህ መንገዶች ብቃት ያላቸውና ዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሆኑ ባለሙያዎችን በማፍራት ከሰው ኃይል ጋር የሚገጥመንን ችግር ለመቅረፍ ጥረት እያደረግን እንገኛለን።

ሁለተኛው ተግዳሮት የበጀት እጥረት ነው። ከዚህ አኳያ በተለይ ምርምርን በሚመለከት የሚገጥመውን የበጀት እጥረት ለማቃለል ዓለም አቀፍ ትብብሮችን በማካሄድ ምርምሮችን እናከናውናለን። ነገር ግን በዓለም አቀፍ ትብብር የሚሠሩ ምርምሮችን ወደ ፊት በይበልጥ አጠናክሮ ማስቀጠል ይኖርብናል። ሌላው ይህ ተቋም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር ነው። ዩኒቨርሲቲው ደግሞ ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ነው። ይሁን እንጂ ተቋሙ በአገሪቱ ጤናው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ስለሚያበረክት ከጤና ሚኒስቴር ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራ ነው። ከሚኒስቴሩ ጋርም በመተባበር ብዙ ሥራዎችን እንሠራለን። ሚኒስቴሩም በተቻለ መጠን በበጀትም ሆነ በሌላ መንገድ ይደግፈናል። በዚህና እነዚህን በመሳሰሉ መንገዶች የበጀት እጥረቶቻችን ለማሟላት እንሞክራለን።

ሌላኛው አንኳር ችግር ተቋሙ የሚሰጣቸው አገልግሎቶችና ተገልጋዮች፣ የትምህርት ፕሮግራሞችና ምርምሮች እየሰፉ ሲሄዱ የመሰረተ ልማት ውስንነት ኢጋጥሟል። ተቋሙ የተገነባው የኢትዮጵያ ሕዝብ 20 ሚሊዮን በሚገመትበት ዘመን ነው። አሁን ላይ የአገሪቱ ሕዝብ ቁጥር ከ120 ሚሊዮን እንደሚልቅ ይገመታል። በዚያው ልክ ተቋሙ የሚሰጠው የሕክምናና የትምህርት አገልግሎት አድጓል። ነገር ግን ተቋሙ ያኔ ሲቋቋም የነበረበት ቦታና ሕንጻ ላይ ነው ያለው። በመሆኑም ያሉብንን የመሰረተ ልማት ውስንነት ለመቅረፍ አንደኛ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ሆስፒታሎችን እንጠቀማለን። ወደነዚህ ተቋማት ባለሙያዎቻችንና ተማሪዎቻችን በመላክ ምርምር ያካሂዳሉ፣ ይሰለጥናሉ፣ የጤና አገልግሎት ይሰጣሉ። በዚህ መንገድ የሆስፒታሉ ባለሙያዎችና ተማሪዎች ሶስቱንም ተልዕኳቸውን ያሳካሉ።

ሌላው ችግሩን በወሳኝነት ያቃልላሉ ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው ሁለት ሕንጻዎችን በግቢው ውስጥ እያስገነባን ነው። እየተገነቡ ያሉት ሕንፃዎች የተመላላሽና የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ሕንጻዎች ናቸው። የሕንጻዎቹን ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ወደ ሥራ ለማስገባት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ሕንጻዎቹ ተጠናቀው ወደሥራ ሲገቡ ያለውን የመሰረተ ልማት ጥበት ያቃልላሉ ተብሎ ተስፋ ተጥሎባቸዋል። ነገር ግን ከችግሩ ስፋት አኳያ ይህ በቂና ዘላቂ መፍትሄ አይደለም። ስለዚህ ከመንግሥት ጋር በመተባበር በመሰረታዊነት ችግሩን የሚቀርፍ መሰረተ ልማቶችን ለማስፋፋት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል።

አዲስ ዘመን:- ሆስፒታሉ ከሌሎች ሆስፒታሎች በምን በምን ይለያል?

ፕሮፌሰር አንዱዓለም:- በአገሪቱ ከሚገኙት ሆስፒታሎች ትልቁና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በመሆኑ፤ ከአራቱ የአገሪቱ ማዕዘን ከሚገኙ የመንግሥትና የግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ለከፍተኛ የሕክምና የሚላኩ ሕሙማንን ተቀብሎ አገልግሎት ይሰጣል። ከዚህ አንጻር ተቋሙ በአገሪቱ የመጨረሻው ከፍተኛ ሕክምና የሚሰጥበት ነው። እንዲሁም በሆስፒታሉ ብቻ የሚሰጡ የሕክምና አገልግሎቶች አሉ። ለአብነት የልብ ቀዶ ሕክምና ከመንግሥት ሆስፒታሎች በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብቻ ነው የሚሰጠው ወይም የሚሠራው። ሌላው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የካንሰር ሕመምን በጨረር የማከም አገልግሎት ቀደም ሲል ከዚህ ሆስፒታል ውጭ በሌሎች አይሰጥም ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ አገልግሎት በጅማ፣ ሀረሚያ እና ሀዋሳ ሆስፒታሎች ተጀምሯል።

ሌላው በጤናው ዘርፍ የድህረ ምረቃ ትምህርት የሚያካሂዱ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች አሉ። እነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርቱን ለመስጠት የሚጎላቸው ነገሮች አሉ። በዚህም ምክንያት ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን እየተቀበልን ለአጭር ጊዜ እናስተምራለን፤ እናሰለጥናለን። ከዚህ ባሻገር የኛ ባለሙያዎች ወደ ዩኒቨርሲቲዎቹ በመሄድ ያስተምራሉ፤ ያሰለጥናሉ።

በተጨማሪም ተቋሙ ያለው የሰው ኃይል ከሌሎች አቻ ተቋማት አንጻር ሲታይ የተሻለ ባለሙያ በብዛትም በስብጥርም አለው። ሆስፒታሉ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስፔሻሊስት ሀኪሞች ካሉባቸው ጥቂት ሆስፒታሎች አንዱ ነው። በተጨማሪም በአገሪቱ የዘመናዊ የሕክምና ታሪክ የመጀመሪያዎቹን ባለሙያዎች ያፈራ ተቋም እንደመሆኑ መጠን፤ በአገሪቱ ውስጥ የጥቁር አንበሳ አሻራ የሌለበት የጤና ተቋም የለም። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም በብዙ ከፍለ ዓለማት ከጥቁር አንበሳ የወጡ ባለሙያዎች በተለያየ የጤና ዘርፎች ተሰማርተው እያገለገሉ ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ዓለም አቀፍ እውቅና ጭምር ያላቸው ናቸው።

አዲስ ዘመን:- ሆስፒታሉ በቀጣይ ስማሳካት ያቀዳቸው እቅዶች ምን ምን ናቸው?

ፕሮፌሰር አንዱዓለም:- አገሪቱ መሪ ወይም የልህቀት ማዕከል ተቋማት ያስፈልጓታል። ከዚህ አንጻር በሚቀጥሉት ዓመታት ተቋሙ ቢያንስ በሁለት ዘርፎች በካንሰር እና በልብ ሕክምና የልህቀት ማዕከል ሆኖ እንዲወጣ ታቅዶ እየተሠራ ነው። ተቋሙ “የልህቀት ማዕከል ነው” ሲባል የትምህርት፣ የጤና እና የምርምር አገልግሎቶችን መስጠት ብቻ ሳይሆን እንደ ሪፈረንስ ሴንተር ሆኖ ያገለግላል ማለት ነው። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ከመላው የአገሪቱ ክፍል ሕክምና ፈልገው ለሚመጡ ታካሚዎች ጥራት ያለውና ላቅ ያለ አገልግሎት መስጠት አንዱ ዋነኛ እቅዳችን ነው።

ሌላው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካንሰር ምዝገባ ማዕከል በተቋሙ ሥር ነው ያለው። ነገር ግን በአገር አቀፍ ደረጃ የካንሰር ምዝገባ ማዕከል የለም። ስለዚህ ተቋሙ በአገር አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ የካንሰር ምዝገባ ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል እየሠራን እንገኛለን። ይህንን እቅድ ለማሳካት ከጤና ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት እየሠራን ነው።

እንዲሁም በሆስፒታሉ የኒኩሊየር ሕክምና ክፍል አለ። በቅርቡም ለዚህ ሕክምና ዘርፍ ወሳኝ የሚባሉ የሕክምና መሳሪያዎችን በመትከል ላይ እንገኛለን። ይህን እያደረግን ያለነው ከዓለም አቀፍ ተቋማት በተለይም ደግሞ ከዓለም አቀፍ የአቶሚክ ኃይል ድርጅት ጋር በመተባበር ሲሆን፤ ዓላማውም ሆስፒታሉን ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች የኒኩሊየር ሕክምና ማሰልጠኛ ማዕከል ለማድረግ ነው ጥረታችን።

ከዚህ በተጨማሪ አሠራራችንን ዲጂታላይዝድ ከማድረግ አኳያ እስካሁን በከፊል ውጤታማ ነን። በቀጣይ ሁሉንም የሆስፒታሉ አሠራሮች፣ አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ እንዲሆን እየሠራን እንገኛለን። በተለይም ደግሞ የራዲዮሎጂ ሥራዎቻችንና መረጃዎቻችን ዲጂታላይዝድ እንዲሆኑ ጥረት አተደረገ ነው። እንዲሁም የሕክምና የከፍያ ሥርዓታችንንም ዲጂታላይዝድ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር በመተባበር እየሠራን እንገኛለን።

ሆስፒታሉ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በውጭ ተመልካቾች ብቃቱን ከማረጋገጥ አኳያ በስፋት ለመሥራት ዕቅድ ተይዟል። ለአብነት የሕክምና ላቦራቶሪያችን በአራት ዘርፎች የብቃት ማረጋገጫ በአገር በቀል የብቃት ማረጋገጫ ተቋም አግኝቷል። በሌሎቹም ዘርፎች ላይ በመሥራት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ጥረት እናደርጋለን። በቀጣይ ደግሞ አገር በቀል የብቃት ማረጋገጫ ድርጅቶች ከሚሰጡን የብቃት ማረጋገጫ በተጨማሪ እራሳችንን በማሻሻል በዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች በመገምገም የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ዕቅድ ይዘናል። ይህም በጤና አገልግሎቱ ብቻ ሳይወሰን በትምህርት ዘርፉ ጭምር አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው። እንዲሁም በቀጣይ እንሠራቢታለን ብለን ከያዝናቸው እቅዶች አንዱ የሕክምና/የጤና አገልግሎት ቱሪዝምን ማስፋፋት ነው። እዚህ ላይም በስፋት እንሠራለን።

በጥቅሉ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከአመሰራረቱ ጀምሮ የሕዝብ ሆስፒታል ነው። ስለዚህ ከሕዝብ፣ ከመንግሥትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተን በመሥራት በቀጣይ ሁሉንም የሆስፒታሉ አሠራሮች፣ አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ እንዲሆን እየሠራን እንገኛለን። በተለይም ደግሞ የራዲዮሎጂ ሥራዎቻችንና መረጃዎቻችን ዲጂታላይዝድ እንዲሆኑ ጥረት አተደረገ ነው። እንዲሁም የሕክምና የከፍያ ሥርዓታችንንም ዲጂታላይዝድ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር በመተባበር እየሠራን እንገኛለን።

ሆስፒታሉ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በውጭ ተመልካቾች ብቃቱን ከማረጋገጥ አኳያ በስፋት ለመሥራት ዕቅድ ተይዟል። ለአብነት የሕክምና ላቦራቶሪያችን በአራት ዘርፎች የብቃት ማረጋገጫ በአገር በቀል የብቃት ማረጋገጫ ተቋም አግኝቷል። በሌሎቹም ዘርፎች ላይ በመሥራት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ጥረት እናደርጋለን። በቀጣይ ደግሞ አገር በቀል የብቃት ማረጋገጫ ድርጅቶች ከሚሰጡን የብቃት ማረጋገጫ በተጨማሪ እራሳችንን በማሻሻል በዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች በመገምገም የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ዕቅድ ይዘናል። ይህም በጤና አገልግሎቱ ብቻ ሳይወሰን በትምህርት ዘርፉ ጭምር አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው። እንዲሁም በቀጣይ እንሠራቢታለን ብለን ከያዝናቸው እቅዶች አንዱ የሕክምና/የጤና አገልግሎት ቱሪዝምን ማስፋፋት ነው። እዚህ ላይም በስፋት እንሠራለን።

በጥቅሉ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከአመሰራረቱ ጀምሮ የሕዝብ ሆስፒታል ነው። ስለዚህ ከሕዝብ፣ ከመንግሥትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተን በመሥራት በቀጣይ እናሳካቸዋለን ብለን የያዝናቸውን እቅዶች እውን በማድረግ የጥቁር አንበሳን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን የጤና አገልግሎት ወደ ተሻለ ምዕራፍ ለማሸጋገር ጥረት እናደርጋለን።

አዲስ ዘመን:- ስለነበርን ቆይታ ከልብ እናመሰግናለን።

ፕሮፌሰር አንዱዓለም:- እኔም አመሰግናለሁ።